# <u>ድንቄም የሰለጠነ ፖለቲካ !</u>

*ሀማ ቱማ*

*ድንቄም የሰለጠነ ፖለቲካ*
*ሕዝብን ለከዳ ጉሮ ወሸባ*

አንደኛው የፋራ ፖለቲካ ነው ሲል ተሳለቀ ፡፡ ለወያኔ እንደ ኢየሩሳሌም ጭቃ፤ እንደ ላስቲክ እጥፍ ዘርጋ፤ ጎበጥ ጎንበስ ብሎ አለመመቸትን፡፡ ሌላኛው ደግሞ ሰሞነኛ ፕሮፌሰር ተብዬ ነውና፤ ሰለጠንኩ ባይ ነውና የሰለጠነ ፖለቲካ የሚለውን ለወያኔም ለፈረንጁም መስገድ ነው በሚል ሳያፍር ተርጉሞ ያልሰለጠኑ ያላቸውን፤ አክራሪ ብሎ ያወገዛቸውን ኢሕአፓና መኢሶንም ሳይቀር በግለሰብ መሪዎች ስም አማካይነት ጠቅሶ ፖለቲካን ይተዉት ሲል በይፋ ተናገረ፡፡ ሌላው ደግሞ ፈረንጇኛ ደብለቅ ማድረጉ አዋቂ ያስመስላል ባይ ነውና አካሄዳችንን እንቀይር ለማለት ፓራዲም ፓራዲም ሲለን ጊዜ አቃጠለ ፡፡ ፋራ የሚለው ቃል አለመሰልጠንን ያመለክታል ተብሏል፡፡ ወደ ሰለጠነ ፖለቲካ ይዘት ከመግባታችን በፊት እስቲ በቅድሚያ ሥልጣኔ ራሱ ምን ማለት እንደሆነ ለመመርመር እንሞክር፡፡

ለእነ ዶክተር ዜሮ መሰልጠን ማለት የነጮች ሎሌና ተከታይ መሆን ነው፡፡ ሰውየው በወላጆቹ ዓለማየሁ እየተባለ "ሊሰለጥን" ፈልጎ አል በሉኝ ይላል፡፡ በራስ ማንነት፤ቀለምና ባህል በማፈር ፈረንጅ ለመሆን መጣሩ መሰልጠን ተብሎ ዳመና ክላውዲያ፤ ዮሴፍና ዮሃንስ ጆ፤ ደብሪቱ ዴቦራ፤ ፍሬህይወት ፊፊ፤ ገረመው ጄሪ፤ እስክንድር አሌክስ፤ ሰሎሜ ሳሊ፤ ሞገስ ሞ፤ አደም አዳም፤ ቆንጂት ኮኒ፤ ዓለማየሁ አል ወዘተ እየተባሉ መሆናቸውን ታዝበናል፡፡ በሀገር ቤት ብዙ ምግብ ቤቶች የፈረንጅ ስም ለራሳቸው መስጠታቸው ሌላ ምሳሌ ነው፡፡ እኛ ልጆች ሳለን ዶሮ ከተለቀ የፈረንጅ ዶሮ ሲባል ዝምብ ከወፈረ ደግሞ ያው የሀበሻ ይባል ነበር፡፡ ራስን ማቅለል፡፡ ይህ ራስን ዝቅ አድርጎ ፈረንጅን ሰማይ መስቀሉ፤ እንግሊዝኛ በመናገር መኩራራቱ፤ የሀገርን ቅርስ ማንቋሸሹ ለነጭ አልገዛም ብሎ ደሙን የገበረውን ትውልድ ታሪክ የሚፃረር አሳፋሪ ክስተት ነበር፡፡ ይህንን በመቃወም ነው በአንድ መልኩ ፀረ ኢምፔሪያሊስቱ ትግል የተፋፋመው፡፡ ያኔም ቢሆን እንደዛሬዎቹ አሜሪካ ይጋልበን ባዮች ለዋሽንግተን የሰገዱና ፈረንጅ አምላኩ የሆኑ ነበሩ፡፡ የተማሪውን የለውጡ እንቅስቃሴ በመቃወም የድሮውን መላሽ ተብለው ተደራጅተው የነበሩት ለምሳሌ በዚህ መልከ የሚጠቀሱ ነበሩ፡፡ ሰለጠነ የሚባለው የራሱን የሀገሩን የተወና የባዕዱን ያደነቀ ና ያዳነቀው ብቻ ነው የሚለው ዛሬም አገርሽቶ እነ አልና ፊፊ እኛን ለወያኔ ና ለፈረንጅ አንሰግድም ያልነውን "ፋራ" ሀበሾችን ሊያወግዙን ተነስተዋል፡፡

መሰልጠን ምንድነው? ከላይ የጠቀስኩት የስም ለውጥ በኢትዮጵያውያን ዘንድ መሰልጠንን ሳይሆን ራስ መጥላትን የሚያመለክት ነው፡፡ በእርግጥ ትምክህት በሰፈነበትና ስሞች በግድ በተቀየሩበት ሁኔታ ወደ የመጀመሪያ መጠሪያ ስም መመለሱ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ አፍሪካን አሜሪካኖች ለምሳሌ የባርነት ስም በሚል ስማቸውን ቀይረው የአፍሪካኖችን ስም መያዝ መርጠዋል፡፡ ማቹ ስቶክሊ ካርማይክል ለምሳሌ ክዋሜ ሴኩ ተብሎ ነበር፡፡ የኬንያው ታዋቂ ደራሲ ጄምስ ንጉጊ ዛሬ ስሙ ተቀይሮ ንጉጊ ዋ ቲዮንጎ ነው፡፡ የኦነግ ዮሀንሶች ዛሬ ዲማ፤ሌንጮና ገላሳ ሆነዋል-- ይህ ግን ምን ያህል ማንታቸውን እንዳሻሻለው ግልፅ አይደለም፡፡ ጆሴፍ ዴዚሬ ሞቡቱ ራሱን ሴሴ ሴኮ ሞቡቱ ካለና ሁሉም ዜጋ የስም ለውጥ እንዲያደርግ ካዘዘ በህዋላ ኮንጎ/ዛይር እንጦርጦስ ወረደች እንጂ አላለፈላትም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ስደት በዝቶ ባለበት የውጭ ሀገር ዜግነት ሲፈለግ ስም ቀይሩ ጫና መኖሩን እናውቃለን፡፡ ግን ተገደው ሳይሆን ወደው የራሳቸውን የተከበረና ትርጉም ያለው ስም ቀይረው ሰለጠንን የሚሉት ፍጡሮች ደግሞ ስለ መሰልጠን ሲያወሩ ብንስቅባቸው መቆጣት የለባቸውም፡፡ ስልጣኔ ሲሉ ስልጣኔ ስንል ብለን በሰፊው ልንፅፍ ብንችልም ወደ ቁምነገሩ ለመመለስ ዛሬ የሰለጠነ ፖለቲካ ተከታይ ነን ለሚሉት አጓጉል ምሁሮች መሰልጠን ማለት ፈረንጅን መከተል፤ ባዕዱን ኮፒ ማድረግ፤ ለባዕድ መስገድ፤ ባዕድን መታዘዝ ሆኖባቸዋል፡፡ ፈረንጅ ራሱን ስልጡን አድርጎ ሲነሳ በተለይ አፍሪካን የጨለማ አህጉር በሚል ሰይሞ አፍሪካኖች አልሰለጠኑም፤ከእንስሳ አይሻሉም ሲል ታሪክን በርዞና ደልዞ መልሶ ለራሳችንም ሲግተን ቆይቷል፡፡ ከሶንግሀይ እስከ አዱሊስ አክሱም ላሊበላ ሐረር ዚምባብዌ ዙሉ ምድር የነበረው ስልጣኔ ተክዶ፤ አፍሪካውያን ባህር ተሻግረው ወደ እስፓኛ ዘልቀው ስልጣኔን ማስፋፋታቸው አይነሳ ተብሎ ወዘተ ፈረንጅ ቅኝ ሊገዛ ሲመጣ ያሰለጠነ አስመስሎ

ያቀርበዋል:: የሰውን ልጅ በባርነት ሊገዙም ሲነሱ ባርያ ያሉትን ክቡር ሰው እንስሳ ማለቱ ክርሰቲያን ነን ለሚለው ህሊናቸው በቂ ሽፋን ሊሰጥላቸው በመቻሉ--በማመቸቱ- እነሱ ባርያ ፈንጋዮቹ ስልጡን ተጠቂው ያልሰለጠነ ተባለ :: ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን ሲወር የጣሊያን ጦር ሀበሻን ሊያሰለጥን ሄደ ተብሎ በካቶሊኩ ጳጳስ ሳይቀር ተባርኮ እንደነበርም የሚታወስ ነው:: ዛሬ በአውሮጳና አሜሪካ ጡት-ደጅ አለባበስን የመረጡት ያኔ የአፍሪካ ሴቶች ጡት መሸፈኛ ባለማድረጋቸው አልሰለጠኑም ባዮች ነበሩ:: የፈረንጅ ታላቅ ደራስያንና ፈላስፎች ሳይቀሩ (ለምሳሌ ጥቀሮች በፍጥረት ከነጭ ዝቅ ያሉ ናቸው ያለው ዴቪድ ህዩም፤ አሳፋሪና ዘረኛ መፅሀፍ የደረሰው ጆሴፍ ኮንራድ ወዘተ) አፍሪካውያን አልሰለጠኑም፤ ቢጎለምሱም አንጎላቸው ሁሌም የህፃን ነው፤ ሰው ይበላሉ፤ ወዘተ እያሉ ራሳቸው አለመሰልጠናቸውን ሲያስመዘግቡ ታዝበናል:: መሰልጠን ፈረንጅ መሆን ከሆነ በእርግጥም የሀገራቸውን ነፃነት አስጠብቀው የቆዩትና በራሳቸው ታሪክና ባህል የኮሩት ኢትዮጵያውያን አልሰለጠኑም ሊባል ይችላል:: ቀደም ሲል ልጠቅስ እንደሞከርኩት ተማሪዎች ሳለን በሀገራችን ና በራሳችን እንዳንኮራና የፈረንጁን እንድናደንቅ በተቃኘው የትምህርት ስርዓት መሰረት አደጋ ተጥሎብናል:: ወደየሲኒማ ቤቱ ጎራ ስንልም የእንግሊዝ ወታደር አፍሪካውያንን ቅኝ ሊገዛ ዘምቶ ሲፈጅ ለ“ነጩ ጎበዝ” እናጨበጭብ ነበር:: የእኔ ትውልድ አብዮት ብሎና ሀገርን ሊያስከብር ሲነሳ ይህን ሁሉ ተቃውሞና ሰብዕናውን ከነጣቂው ለማስመለስም ነበር:: ከ 40 ዓመት በህዋላ በነጩ ትምህርት ቤት ያን የዱሮውን መርዝ ተግተው ራሳቸውን የጠሉ ዶክተሮችና ፕሮፌሰሮች ብቅ ብለው ፈረንጅ አምላኩ፤ፈረንጅ ይግደለን ባይ ሲሆኑ መታዘብ መቻም አሳዛኝ ነው:: የሰለጠነ ፖለቲካ የሚሉን ደግሞ ዝርዘሩ ሲታይ ሲመረመር እርባና ቢስ መሆኑን ከዚሁ መገመት ይቻላል::

ቅኝ ገዢዎች ሆኑ ማንኛውም ገዢ መደብ የራሱን የበላይነት ለማስጠበቅ የራሱ ሀሰቶችን በእውነታ ደረጃ ሰይሞ ህዝብን ለማሳመን መጣሩ የሚጠበቅ ነው:: ፈረንጆች አፍሪካውያንን ዝቅተኞች ናችሁ ብለው በማሳመን በባርነት ደረጃ ሊገዙ ችለዋል:: ዛሬም ቢሆን ይህ የዝቅተኝነት መንፈስ የአፍሪካውያንን አንጎል መርዞ መገኘቱና እየጎዳንም መቆየቱ የሚካድ አይደለም:: በምዕራብ አፍሪካ አንድን ሰው አዋቂ ለማለት ከነጮች እግር ስር ቁጭ ብሎ የተማረ ነው ብሎ ማዳነቅ የተለመደ ነው:: ወያኔን ብንወስድ ዘረኛ አገዛዙን ለማስፈን ህዝብን እርስ በርስ ከፋፍሎ ያባላል:: አማራ የተባለ ጭራቅ መጣብህ ብሏቸው ይህንኑ አምነው ዛሬም በጥላቻ የሚወዘወዙ ጥቂት አይደሉም:: የትግራይ ወጣቶችንም ሆነ ህዝብ በአጠቃላይ ወያኔ ከተወገደ በትግራይ ህዝብ ላይ መዘዝ ይመጣል ብሎ ሲሰብክ የሰማነው ነው:: ይህንኑ አምነው “ትግሬ እየገዛ ነው” ብለው ከወያኔ ጎን አለና የሚሉ የትግራይ ተወላጆችም የሉም ማለት ከቶ አይቻልም:: የበላይነትም ሆነ የዝቅተኛነት ስሜት፤ ጥላቻ ወዘተ ተኮትኩቶ ያድጋል:: አገልጋይነቱ ደግሞ ላቀደውና ላለመው ነው:: በዚህም መሰረት ነጮች/ገዢዎች እኛ አፍሪካውያን በራሳችን ላይ እምነት እንድናጣ በዘመኑ አነጋገር አንጎላችንን ያጥቡታል ፤ ማለትም የፈለጉትን ያሳምኑናል:: እንደ ሞኝ ስድብ ተቀብለን ራሳችንን እንሰድባለን:: በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ የሕዝብ የነፃነት ትግል ማንነቱን ለማስመለስና ለማረጋገጥ ነው ስንል በራሱ ታሪክና ባህል ኮርቶና አንገቱን ቀና አድርጎ፤ በራሱ ስልጣኔ አምኖ ሊኖር ፍላጎቱንም ለማመልከት ነው:: ታዲያ ስማቸውን ቀይረው አል፤ ቴዲ፤ ኢላይ ወዘተ እስከማለት የደረሱት--የወረዱት-ነጭ አምላኩዎች ይህን ዓይነቱ ትግል ባይገባቸውና በሰለጠነ ፖለቲካ ሽፋን ለነጭም ለነፍጥም መገዛትን ቢሰብኩ ምን ያስገርማል?

በራስ መተማመን ታሪክን ቅርስን ማክበር ትምክህት አይደለም:: ሌላን መናቅ ወይም ኢፍትህዊነትን ማቀፍም ጋር አይገናኝም:: አጉል መኩራራትንም አይጠቀልልም:: ተገዢነትን ግን ይቃረናል:: ለባዕዳን ማጎብደድን ሆነ ለጨቋኝ አንገት ደፍቶ መገዛትን ይቃወማል:: ይህ በራስ የመተማመንና በታሪክ የመኩራት መንፈስ ጠንካራ ስለነበር ነው የሀገራችን አርበኞች “የሰለጠነውን” የጣሊያን ጦር በዘመናዊ መሳሪያና ትጥቁ በልጦናል በሚል ያልተንበረከኩለት:: ጣሊያን ጥቁሮች ሁሉ ዝቅተኛ ፍጡሮች ናቸውና ልገዛቸው ይገባኛል ሲል ኢትዮጵያውያኖች/ ከባንዳዎች በስተቀር/ ይህን ተቀብለው አንገታቸውን አልደፉለትም፤አልሰገዱለትም:: ተዋጉት እንጂ:: መሰልጠን ማጎብደድ ሆኖ ዛሬ በፖለቲካው መስክ ሲውገረገርብን ከርዕዮት ጀምሮ ራስን መካድን ያንፀባርቃል:: ለሰው በላና ለተበሻቀጠ ስርዓት ማርገድ ማሳፈሩን ይክዳል:: ለህዝብና ለሀገር ብለውና በተለይም ባዕድ--አሜሪካ ተባለ ሩስያ--ሀገራችንን አይደፍርም በሚል የታገሉትን እንቅስቃሴዎችንም መወንጀልና ማውገዝን ያሰፍናል:: በዛሬው ዓለም አንድ ሀያል መንግስት አለና እሱ ባለውና በወሰነው ብቻ መንጎዱ ብልህነት ተብሎ፤ መሰልጠን ተብሎ

ይፈረጃል፡፡ ህፃናትን በቦምብ እየፈጀ ያለው የሰለጠነ ሀገር መሆኑ ነው! ይህ አምልኮተ ባዕድ ከመሰልጠን ተቀናጅቷልና አልፎ ተርፎ በአሜሪካ ባለው መሰረት ከሁለት የፖለቲካ ፓርቲ ውጪ ሀገራችን አያስፈልጋትም ሲባልም አድምጠናል፡፡ መሰልጠን ራስን መካድና መናቅ ሆኖ የእናት አባት ቋንቋን ልጆች እንዳይማሩ ተደርጎ፤ በሁሉም መስክ የፈረንጁ ባህል ተቀድቶ ማንነታችንን እየሰረዘ መሆኑ ደግሞ ክርክር አያሻውም፡፡ ምሁርነትም (ቀይም የሰለጠኑት እንደሚሉት ሊህቅነት) በግልቡ ተወስዶ በከብት ህክምና ዶክተር ስለተባለ በፖለቲካ ላይ ቀዶ ጥገና ማካሄድ የሚችል ይመስለዋል፡፡

ፋራ ፖለቲካ የተባለው ለወያኔ አለማጎብደድ ሆኖ የሰለጠነ ፖለቲካ የተባለውን ደግሞ ስናየው ምንም አዲስ ተዓምር ይዞ ያልመጣ ያው እጅ እጅ ያለውን እጅ መስጠትን የሚያነግስ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የሰለጠነ ፖለቲካ ማለት የህዝብን አድማ በፈረንጅ ትዕዛዝ ማክሸፍ፤ የህዝብን ትግል ማዳከም፤ ህዝብን መናቅ፤ ተምረናል ብሎ ህዝብና የእኔ ብጤን መናቅ፤ ዛሬ ደግሞ ከባዕድ ጋር በማሴር ድርጅቴ ያሉትንና የህዝብን ትግል ከአፈር ለመደባለቅ መራወጥ ማለት ነው፡፡ እኛ ያልሰለጠነው የፖለቲካ ሰዎች ደግሞ ዛሬም ቢሆን የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያ ጠላት ነው፤ ለአሜሪካ አንሰግድም፤ በህዝባችን ላይ በባዕድ ታዘን አንቀልድም ስለምንል ከመ አርዮስ እየተወገዝን ነው፡፡ በኢሕአፓ ላይ በአሁኑ ጊዜ እየተካሄደ ያለው የስም ማጥፋት ዘመቻ ተዛምዶ የሰለጠነ ፖለቲካ አራማጆች ነን የሚሉት ትላንት መሪዎቻችን ይሏቸው የነበሩትንም ማጥቃት ተያይዞታል፡፡ የሰለጠኑ ፖለቲከኞች በአሜሪካ ትዕዛዝ ለመለስ ሰግደው በመጪው የወያኔ የምርጫ አስረሽ ምቺው ላይ ዳንኪራ ሊረግጡ ከወዲሁ ጫማ መወልወል የጀመሩት ናቸው፡፡ የሰለጠነ ፖለቲካ በሰማዕት ደም ይቀልዳል፡፡ የሰለጠነ ፖለቲካ ክህደትን ያስቀድማል፡፡ የሰለጠነ ፖለቲካ የፋራ ሳይሆን የፈሪዎች ነው፡፡ አድርባይነት ነው፡፡ ከህዝብ ጠላት ያስተቃቅፋል፡፡ ለዚህም ነው በአሁኑ ወቅት የሰለጠኑ ፖለቲከኞች በዋሽንግተን ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አጋፋሪነት ከህዝብ ጀርባ ሲያሴሩ እየታዩ ያሉት፡፡

መማር መሰልጠን ይህ ከሆነ ባልሰለጥን ባልማር ይቅር የሚሉ ግትሮች ብዙ ቢሆኑም አንዳንዶች ደግሞ ከስልጣኔው አይቅርብን ሊሉ መነሳታቸው ስለማይቀር ለመሰልጠን የሚያስፈልጋቸውን ሳልጠቁም ማለፉ ትክክል አይሆንም፡፡ የሰለጠነ ፖለቲካ ለማካሄድ ሰበርበር ቢልም እንግሊዝኛ መናገር ወሳኝ ነው፡፡ ከስም ፊት ደግሞ ዶክተር ፕሮፌሰር የምትለዋ ቅፅል/ከየትም ትገኝ ከየት/ ካለች ስልጣኔው ጦፈ ማለት ይቻላል፡፡ በአዲስ አባባ ከሆነ ወደ አሜሪካ ኤምባሲ፤ በአሜሪካ ከሆነ ደግሞ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ብቅ ማለትን ማዘውተሩ ደግሞ ሸጋ ነው፡፡ የሀገርን ታሪክ ናቅ ማድረጉ፤ ስምን ፈረንጃዊ ቃናና ይዘት መስጠቱ (ድርቅ ብሎ  ወርቅነሽ መባልን ትቶ ጎልዲ መሆን) ፤ ልጆችን  የሀገር ቋንቋን ማስተማርን መቃወሙ፤ የፈረንጅን ባህል መቅዳቱ፤ የህዝብን የትግል ታሪክ ፋራና ስህተት ብሎ ማውገዙ፤ በቡሽ ሞት ብሎ መማሉ፤ ኢሕአፓን ነጋ ጠባ ማውገዙ፤ መቻቻል የሚለውን ቃል ማነብነቡ፤ ካመቸና ከሆነ ደግሞ በሼራተንና ሂልተን ከእነ በረከት ጋር ብርጭቆ ማጋጨቱ፤ ክትፎ አልወድም የጣሊያን ካርፓቾ ነፍሴ ነው ብሎ መመፃደቁ፤ ለህዝብ ብዬ እንጂ እኔ እኮ የናጠጥኩ ሀብታም ነኝ ብሎ መፎከሩ፤ በየንግግሩ "አክችዋሊ አዲስ ፓራዲም ያስፈልጋል ዌክ አፕ ማን" ማለቱ ደግሞ የግድ ነው፡፡ የሰለጠነ ፖለቲካ ተከታዮች በጣሊያን ወረራ ጊዜ በርክተው በነበር በቪቫ ዱቼ ጩኸት ሀገራችን ትታመስ ነበር፡፡ መሰልጠን ከባድ ነውና የሰለጠነ ፖለቲካ ሊያካሂዱ የሚያስቡ ሳይታክቱና የህዝብን ቁጣ ሳይፈሩ መጣር አለባቸው፡፡ ዓይንን በጨው ኡጥቦ ህዝብን መካድ፡፡ከዚህ ሌላ ደግሞ በብድርም ሆነ በሌላ የተወሰነ ዶላር ይዞ ወደ ሀገር ዘልቆ በእኔ ብጤው ላይ ማነጀብና መለስተኛ አላሙዲ መሆን ስልጡን መሆንን ያረጋግጣል፡፡ መራራ ትግል ለሚሉት ደግሞ ትግል ሲመር በኬክ አድገናልና አይጥመንም ብሎ መመለሱና ማሳፈሩ የሰለጠነ ፖለቲካ መለያ ነው፡፡ ፖለቲካን ድብልቅልቁን ማውጣት ደግሞ ባይመስልም የሰለጠነ ፖለቲካ ዋናው እምብርት ነው፡፡ ከፊታቸው ጠመንጃ ተደግኖ ግንባራችን አይታጠፍም የሚሉ ግትሮችን አጋልጦ ከትግሉ ጎራ በማስወገድ ለስለስ ቀለስለስ ያለን የሰለጠነ ፖለቲካ ማስፈንን መምረጥ ደግሞ ወሳኝ ነው፡፡ አንዳንዶች የሰለጠነ ፖለቲካን ለማካሄድ አለመሰልጠንና መደንቆር ያስፈልጋል ብለው ሊያሾፉ ቢፈልጉም የሰለጠነ ፖለቲካ መፈክሩ ፈሪ ለእናቱ፤ ከመሞት መሰንበት፤ ከሞተ አንበሳ ያለ እንስሳ፤ ከራስ በላይ ነፋስ፤ከጀርባ ሆድ ይቀርባል፤የተከፋ ተደፋ፤ ዳገት እርሙ ሜዳ ወንድሙ ዓይነቶቹ ናቸው፡፡ ቀሰ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል ተወዳጅ ነው፡፡ ወያኔን በትዕግስት ከያዝነው አንድ ቀን ስልጣን ይለቅልን ይሆናል ብሎ ማመን ተገቢ ነው፡፡ በይፋ ስንናገር ስንቀሰቅስ ደግሞ ይሉኝታን መጀመሪያ ማፈን መግደል ያስፈልጋል፡፡ ባደረግነው ቅስቀሳ የተነሳ የዋሆች ተሰልፈው የአገዛዙ ጥይት ሰለባ ከሆኑ ደግሞ በእንግሊዝኛ "ቱ ባድ" ብሎ ማለፍ መቻል

ያስፈልጋል። ገንዝብን መጥላት ደግሞ ከሰለጠነ ፖለቲካ ጋር ያራርቃል፤መርህ አለኝ ብሎ መድረቅም እንዲሁ።

የሰለጠነ ፖለቲካ? የምን ሀገር፤የምን ህዝብ፤ የምን ፅናት፤ የምን ቃልኪዳንና መርህ?
ሆድ ይቅደም ነው ዋናው።